# አንድ ቃል ስንት ነው?

ማነህ ባለ ቅኔ? ማነህስ ገጣሚ?
አንት የውበት አዳኝ የሕይወት ተርጉአሚ፣
ከቡር ባለ ቅኔ የኑሮዬ አድማቂ፣
በሰው ሃዘን አልቃሽ በሰው ደስታ ሳቂ፤
እስቲ ልጠይቅህ መልስህ ይፈለጋል፣
አንድ ቃል ስንት ነው? ስንት ነው አንድ ቃል?

ስሎሞን ሞገስ

..../// ........

"አንድ ቃል ስንት ነው" ብለህ ለጠየከው፣
ያነቡታል እንጅ ከልብ ላይ ጥፈው፣

አይዘረዝሩትም ቃል አይደለም ብር፣

አይሽከሽኩትም ካርድ አይደለም ቃል።

ቃል ሰውነት ነው - ሰውነት ነው ቃሉ፣

ከሰሎ ይዘልማል - ጥልቅ ነው ሚስጥሩ፣

ልብና ህሊና አንድ እምነት ነው ቁጥሩ!!

(ሙሉቀን)

…..//////……

አንድ ቃል እልፍ ነው እልፍ ያዳነ ለታ፣
የሳት ሰደድ ሆኖ በእምቢታ ሲፈታ::
ከጽንሰቱዋም በፊት ምድር ሳትፈጠር፣
ቃሌ የተባለ የቃል ጉልበት ነበር::
አንድ ቃል ሰልጥኖ.....
ጨለማን ከጥልቁ ከውስጡ መጥኖ፣
ይሁን ብርሃን ሲል አንድ ቃል እልፍ ሆኖ፣
ባንድ ቃል ተምጠን፣
ባንድ ቃል ተፈጥረን፣
ባንድ ቃል ተቆጥረን፣
ባንድ ቃል ከገነት እመቀመቅ ወርደን፣
ደሞ ስለ-አንድ ቃል አንድ ቃል አነቀን::

ሂኖክ የሽጥላ

………./// ……..

'ሚቆዘም 'ሚታወስ 'ሚወደስ፣
የአላማ ፅናትን 'ሚያስዳስስ፣
ቁርጠኝነትን 'ሚያድስ፣
ቃል፤
ጀግናን ዕቶን ውስጥ 'ሚዶል፣
ቃል፤
ስቃይ መከራን 'ሚያስችል፣
ቃል፤
የጀግኖች ብሩህ ተስፋን 'ሚያግል፣

ቃል .....

ዓለማየሁ ላቀው
በዕለተ ማርያም የካቲት 21 2004 ተፃፈ